# የሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ (SDOT) የ2023 ምርጥ

## እነዚህ የእኛ ከፍ ብለው የጎሉ ናቸው



ግሬግ ስፖትስ
ዳይሬክተር፣ የሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ

ሃሎ ሲያትል! እኔ ግሬግ ስፖትስ (Greg Spotts) ነኝ፣ የሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ ዳይሬክተር። በ2023 ውስጥ፣ ከ100 በሚበልጡ የማህበረሰብ የማዳመጥ ጉብኝት ዝግጅቶች ላይ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ሰዎች ሰምቻለሁ። የ SDOT በዓመቱ ውስጥ የጎሉ የተባሉ ግምገማዎች እነሆ!

ጥር ውስጥ፣ ለሲያትል የህዝብ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች ነጻ የሕዝብ መጓጓዣ መሳፈሪያ ማለፊያዎችን ሰጥተናል። የካቲት ውስጥ፣ የደህንነት ፕሮግራሞቻችንን ሙሉ ግምገማ አሳትመናል።

በበጋው የግንባታ ወቅት፣ ትላልቅ እና ትናንሽ ፕሮጀክቶችን አጠናቅቀናል። እነዚህ ፕሮጀክቶች በእግር ለመሄድ፣ ብስክሌት ለመጋለብ እና የሕዝብ መጓጓዣ ለመጠቀም የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ ያደርጉታል። ነሐሴ ውስጥ፣ የሲያትል የመጓጓዣ እቅድ ረቂቅ አሳትመናል። ይህ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት የምናውላቸው መዋዕለ ንዋዮቻችንን ለመምራት ይረዳል። ጥቅምት ውስጥ፣ የማርቲን ሉተር ኪንግ (MLK) የደህንነት ፕሮጀክት የግንባታ መሠረት አኖርን። ይህ በደቡብ ሲያትል ውስጥ ካሉት አራት ዋና ዋና የብስክሌት መስመር ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው ነው።

የአውቶቡስ ጉዞን ለማሻሻል፣ RapidRide H መስመር ወደ ምዕራብ ሲያትል ከፍተናል። እንዲሁም ወደ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የሚወስደውን መስመር 44ንም አሻሽለናል። በ2024 ውስጥ፣ የRapidRide G መስመር ፕሮጀክትን እናጠናቅቃለን እና የRapidRide J መስመር ግንባታ እንጀምራለን። እንዲሁም የጭነት ማንቀሳቀስ ለመቀጠል እና ቀረጥ (Levy) ለMove Seattle አጠንክረን ለመጨረስ East Marginal Wayን እናሻሽላለን።

በ2024 ውስጥ ከፊታችን ያለውን ስራ ለመጀመር፣ ከእናንተ ከሲያትል ማህበረሰባችን ጋር በሽርክና በመተባበር ለመጀመር መጠበቅ አያስችለኛም።

አመሰግናለሁ እና መልካም አዲስ ዓመት!

# እንዴት ተገናኝቶ መቆየት እና እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ እነሆ!

**ይጎብኙ:** www.seattle.gov/transportation
**ይደውሉ:** (206) 684-ROAD (7623)
**ኢሜይል:** 684-ROAD@seattle.gov
**ያንብቡ:** sdotblog.seattle.gov/
**ይከታተሉ:**www.seattle.gov/transportation/about-us/contact-us

Seattle Department of Transportation

## ደህንነትን ወደፊት ለማስኬድ እርምጃ ወሰደናል

**98** አዲስ የእግረኛ የመጀመሪያ ምልክቶችን ገቢር አድርገናል!

## ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶቻችንን ወደፊት ወሰደናቸዋል

**25** ፕሮጀክቶችን ንድፍ አውጥተናል።

የ **13** ፕሮጀክቶች ግንባታ ጀምረናል።

**13** ፕሮጀክቶች ጨርሰናል።

## ቀረጥ ለMove Seattle ፕሮጀክቶች ላይ ውጤቶች አግኝተናል

**11** የመንገድ መስመር-ማይሎችን ዘርግተናል።

**26** የእግረኛ መንገዶች ብሎኮችን እንደገና ወደነበረበት መልሰናል።

ለልጆች ወደ ትምህርት ቤት በእግር እንዲሄዱ፣ ለማንከባለል እና በብስክሌት ለመጋለብ የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ

**26** ፕሮጀክቶችን ጨርሰናል።

*እነዚህ የቁጥር መረጃ ጥናቶች እስከ መስከረም 2023 ድረስ ያሉ ናቸው።

## የደንበኞች አገልግሎት ጥያቄዎችን በላቀ ሁኔታ ሸፍነናል

**19,200+** ጥያቄዎች እና አሳሳቢ ጉዳዮችን በሕዝብ የስልክ መስመራችን በኩል አስተናግደናል።

## በሲያትል የመጓጓዣ ጉዳይ ማህበረሰቡን አሳትፈናል እቅድ

**4,500+ ይዘናል**

የተጋጋሉ ውይይቶችን ከህዝብ ጋር።

ለማደግ ለምትታትር ሲያትል

**8,000+** ሀሳቦች ተቀብለናል!

## ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተናል

በአንድነት ተዳምሮ **$65** ዶላር ሚሊዮን የፌዴራል እና የስቴት የገንዘብ ድጋፎችን አግኝተናል።



## ደቡብ ሲያትል ውስጥ የደህንነት እና የብስክሌት ፕሮጀክቶችን ወደፊት አስኪደነዋል

ቡድናችን ጠቃሚ በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ እድገት አድርጓል። እነሱም Beacon Hill፣ East እና West Marginal መንገዶች፣ ከGeorgetown ወደ ደቡብ ፓርክ፣ ከGeorgetown እስከ መሃል ከተማ፣ እና MLK Jr Way Sን ያካትታሉ።



## በAurora Avenue North ላይ ደህንነትን እንደገና አሰበናል

ቡድናችን ስለ Aurora Ave N የተሻለ ደህንነትን ለመገመት ከማህበረሰቡ ጋር ተወያይቷል። እንዲሁም የእግረኛ መንገዶችን ብሎኮችን አሻሽለዋል እና የመንገድ ዛፎችም በመልካም ሁኔታ የተጠበቁ አድርገዋል።



## ድልድዮቻችንን እንደተጠበቁ አቆይተናል

ቡድናችን በመላው ከተማ ውስጥ ያሉትን ድልድዮች ጠግኖ አቆይቷል። ይህ በ2023 መጀመሪያ ላይ፣ የበረዶ አውሎ ንፋስ ጉዳት ከደረሰ በኋላ፣ የSpokane St Swing ድልድይ (ዝቅተኛ ድልድይ) ለመጠገን የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ምላሽን ያካትታል።




## ደህንነትን ወደፊት ለማስኬድ እርምጃ ወስደናል

ቡድናችን የደህንነት ፕሮግራሞቻችንን በሙሉ ግምገማ አጠናቅቋል። እንድሁም በመላው ከተማ ከ 70 በላይ አዳዲስ በቀይ ማብራት መታጠፍ ክልክል ነው ምልክቶችን ጨምሮ ላቅ ያሉ እርምጃዎችን ወስደናል።



## አዳዲስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ፈትሸናል

ቡድናችን የSDOT ብዛት የላቸው ተሽከርካሪዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ የብስክሌት መስመር ጠራጊያዎችን እና ሌሎችንም በኤሌክትሪክ ኃይል እንዲሰሩ ለመጀመር የሙከራ ፕሮግራሞችን አስፈንጥቀዋል።



## የሕዝብ መጓጓዣ ልምዱን ቀይረናል

ቡድናችን የRapidRide H መስመር አገልግሎትን ከፍቷል። በ RapidRide J መስመር እና መስመር 40 ፕሮጀክቶች ላይ የንድፍ ሥራውን አጠናቅቀናል። በMadison RapidRide G መስመር ግንባታ ለመጨረስ 75% ደርሰናል።

# ወደ 2024 ፊታችንን ሰናቀና

በእድገት እና በዓላማ የተሞላ አዲስ ዓመት እየጀመርን ነው! በመራጭ-የፀደቀ ቀረጥ (Levy) ለMove Seattle የመጨረሻ ዓመት ውስጥ ስንገባ፣ ትኩረታችን ጠንካራ ነው። በከተማው በመላ ፍትሃዊ እኩልነት፣ ተፅእና ፈጣሪነት ያላቸውን ፕሮጀክቶች እናቀርባለን።

ለተጨማሪ ነዋሪዎች የተሻሉ የሕዝብ መጓጓዣ አማራጮችን በሚያቀርበው፣ የRapidRide J መስመር ፕሮጀክት ላይ መሠረት እናኖራለን። ባላርድ ውስጥ የደህንነት ማሻሻያዎች ግንባታ እና የንጣፍ መዘርጋት ስራ እየጀመርን ነው። እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ ሲያትል በRainier Ave S ላይ የአውቶቡስ መስመሮችን እያራዘምን ነው። ደግሞም በማዕከላዊ ሲያትል የሚገኘውን የMadison RapidRide G መስመር ፕሮጀክትን እናጠናቅቃለን!

ደህንነት በቀዳሚዎቻችን ከፍተኛው ሥፍራ ላይ ይቀመጣል። ተጨማሪ የእግረኛ-የመጀመሪያ ምልክቶች እና በቀይ ምልክቶች መታጠፍ ክልክል ነው የሚሉትን እያስገባን ነው። እንዲሁም የብስክሌት መንገድ መስመሮቻችንንም እያጠናከርን ነው። ይህ ለእያንዳንዱ ሰው ደህንነትን ይጨምራል! የእኛ የ2024 ጭብጥ መልእክት: "ደህንነታቸው የተጠበቀ መንገዶችን ማድረስ" ነው።

የአየር ንብረት ቀውስን መታገል አንድ ዋና ዐቢይ ግብ ነው። ልቀቶችን ለመቀነስ እና የአየር ንብረት ግቦቻችንን ለማሳካት ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማግኘት እየሰራን ነው። ከንግዶች፣ ለትርፍ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ እና ከሌሎች የህዝብ ተወካይ ድርጅቶች ጋር አጋርነት/ ሽርክና እናደርጋለን።

ይህንን ብቻችንን ማድረግ አንችልም። እነዚህን ራዕዮች ወደ እውነት ስንቀይር የእርስዎን ተሳትፎ ለማየት በጉጉት እንጠባበቃለን። ከናንተ አንድ የሲያትል ማህበረሰብ ከሆናችሁት ጋር፣ የከተማዋን የማመላለሻ ስርዓት መለወጥ እንችላለን።

ሙሉውን የሲያትል የመጓጓዣ እቅድ እናትማለን



በመራጭ-የፀደቀ ቀረጥ (Levy) ለMove Seattleን በተጠናከረ መልክ እንጨርሰዋለን



በመላዋ ከተማ የሕዝብ ማመላለሻዎችን እናሰፋፋለን

